መልእክተ ፡ ዮሐንስ ፡ ዳግሚት ።

ሁለተኛዪቱ ፡ የዮሐንስ ፡ መልእክት ።

ቀዳማዊ ፡ ብሎ ፡ ነበረና ፡ ዳግሚት ፡ አለ ፡
ሁለተኛ ፡ ይጽፉል ፡ ሞግዚት ፡ ሆና ፡ በደ
ሴት ፡ ልብስ ፡ ቀለብ ፡ እየተቀበለች ፡ የነ
ገሥታቱን ፡ የመኳንንቱን ፡ ልጆች ፡ የ
ምታሳድግ ፡ ሮምና ፡ የምትባል ፡ ሴት ፡ ነ
በረች ፡ ዮሐንስና ፡ አብሮኮሮስ ፡ የሚገ
ቡበት ፡ ምክንያት ፡ ቢያጡ ፡ ያባቷ ፡ የቅ
ድመ ፡ አያቷ ፡ ባሮች ፡ በጠፋን ፡ በብዙ ፡
ዘመናችን ፡ ተገኝተናል ፡ እያሉ ፡ ያስወሩ ፡
ዠመር ፡ እሷም ፡ ውዳሴ ፡ ከንቱ ፡ ሽታ ፡
አዎን ፡ የአባቴ ፡ ያያቴ ፡ ባሮች ፡ ናችው ፡
ይግቡልኝ ፡ ብላ ፡ አስገብታቸዋለች ፡ ዮሐ
ንስን ፡ ለቤተ ፡ ብለኔ ፡ ዕንጨት ፡ ፈላጭ ፡
እሳት ፡ አንዳጅ ፡ አብሮኮሮስን ፡ መንቀል ፡
አጣቢ ፡ አድርጋዋለች ፡ የሄዱበት ፡ ለማስ
ተማር ፡ ነውና ፡ ሁሉም ፡ ባያሉበት ፡ ሥራ
ቸውን ፡ እልአከናወኑም ፡ ከዕለታቱም ፡ ባ
ንድ ፡ ዕለት ፡ ከምታስተምራቸው ፡ ልጆች ፡
አንዱን ፡ አስከትላ ፡ ከቤተ ፡ ጣዖት ፡ ገባች ፡
እነሱም ፡ ተከትለዋት ፡ ሄዱ ፡ በነሱ ፡ አ
ድሮ ፡ ያለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡
በጣዖቱ ፡ አድሮ ፡ ያለ ፡ ሰይጣን ፡ ወጥቶ ፡
እሄዳለሁ ፡ ሲል ፡ የተከተላትን ፡ ብላቴና ፡
ረግጦ ፡ ገደለው ፤ ወደ ፡ ኋላ ፡ ተመልሳ ፡
ብታይ ፡ ተከትለዋት ፡ አየች ፡ እሊህ ፡ ከ
መጡ ፡ ዠምሮ ፡ ኀዘን ፡ እንጅ ፡ ደስ ፡
ብሎኝ ፡ አላውቅም ፡ ብላ ፡ ዮሐንስን ፡ በጥፊ ፡
መታችው ፤ እስነሡት ፡ ይባላል ፡ እንጅ ፡
ሰው ፡ ይመታልን ፡ አላት ፡ ደግሞ ፡ ሰው ፡
ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ይነሣል ፡ ብላ ፡ እደግመዋ
ለሁ ፡ ስትል ፡ አድርጋችሁ ፡ አሳዩኝ ፡ ይባ
ላላ ፡ አላት ፡ በሉ ፡ አስነሡት ፡ አለቻ
ቸው ፡ ወዲያው ፡ ጸልየው ፡ አስነሥተው
ታል ፡ ማን ፡ ገደለህ ፡ ብትለው ፡ በዚህ ፡
አድሮ ፡ ያለ ፡ ዐይኑ ፡ ፈጣጣ ፡ ጥርሱ ፡ ገጣ
ጣ ፡ እሊህን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ወጥቼ ፡ እሄዳ

ለሁ ፡ ሲል ፡ ረግጦ ፡ ገደለኝ ፡ እሊ
ህስ ፡ አስነሡኝ ፡ እንጅ ፡ ምንም ፡ አላ
ሉኝ ፡ ብሎ ፡ መስክሮላቸዋል ፤ እሷዋም ፡
አላበጀሁም ፡ ብላ ፡ ከእግራቸው ፡ ወድቃ
ለች ፤ ላጭተው ፡ አሳምነው ፡ አጥምቀው ፡
በዚያው ፡ ባለችበት ፡ እመ ፡ ምኔት ፡ ሹመ
ዋት ፡ ሂደዋል ፡ ከሄዱ ፡ በኋላ ፡ ሲያጸና ፡
ጽፎ ፡ ይሰድላታል ፡ የጻፈበት ፡ ሀገር ፡
በመካከል ፡ ክታብ ፡ ወሳጅ ፡ የለም ፡ ምክ
ንያት ፡ ሞገስ ፡ ወሰላም ፡ ወምሕረት ፡ ቍ ፡
፫ ፡ በል ። ተፈሣሕኩ ፡ ጥቀ ፡ እስመ ፡ ረከ
ብኩ ፡ በል ፡ ቍ ፡ ፬ ። እስእለኪ ፡ አእግዝ
እት ፡ በል ፡ ቍ ፡ ፭ ። ዑቁ ፡ ርእሰክሙ ፡
በል ፡ ቍ ፡ ፰ ። ወዘኒ ፡ ይመጽእ ፡ ኀቤክ

፣ ዮሐንስና ፡ አብሮኮሮስ ፡ ሮምናን ፡ ተከትለው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ጣዖት ፡ እንደ ፡ ገቡ ።

www.ethiopianorthodox.org

ሙ ፡ በል ፡ ቍ ፡ ፲ ። ወብዙኅ ፡ ብየ ፡ በል ፡ ቍ ፡ ፲፪ ። ይኤምኑኪ ፡ በል ፡ ቍ ፡ ፲፫ ።

፩ ፤ እምነ ፡ ቀሲስ ፡

ከኔ ፡ ከቄሱ ፡ ከዮሐንስ ፡ የመጣች ፡ ክታብ ። ሐተታ ፡ እስከ፡ ሊቀ፡ ጳጳስነት ፡ ያለ፡ መዓርግ ፡ ተሰጥቶት ፡ ሳለ ፡ እምነ፡ ቀሲስ፡ አለ ፡ ስለ ፡ ትሕትና ። አንድም፡ እምሊቅ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ኀረይ ፡ ሰብዓ ፡ ቀሲሳነ ፡ እንዲል ፡ ሊቃውንተ ፡ ሲል ። አንድም ፡ በበለጠ ፡ መዓርጉ ፡ ተናገረ ፡ ቀሲስ ፡ ማለት ፡ አበ ፡ ሕዝብ ፡ መገሥጸ ፡ ሕዝብ ፡ መሥተስርየ ፡ ሕዝብ ፡ ማለት ፡ ነው ፡

ለኅሪት ፡ ወለእግዝእት ።

ኅሪት ፡ ስሟ ፡ ነው ፡ ለመቤቴ ፡ ለኅሪት ፡ ትድረስላት ። ሐተታ ፡ አሁን ፡ ከእኔ ፡ ዘንድ ፡ የነበረ ፡ ብላቴና ፡ ምን ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ ደረስና ፡ እንዲህ ፡ ይለኛል ፡ እንዳትለው ፡ በቀደመ ፡ ስሟ ፡ ጠራት ፤ እናንተም፡ ጌቶቻችሁን፡ በቀደመ ፡ ስማቸው፡ ጥሯቸው፡ ለማለት ፡ ለአብነት ። አንድም፡ ለኅሪት፡ለጥምቀት ፡ ሲል ፡ ነው ፤ ወለእግዝእት ፡ በጥምቀት ፡ ባገኘችው ፡ ኀይል ፡ አጋንንትን ፡ ለምትገዛ ፡ ድል ፡ ለምትነሣ ፡ ትድረስላት ፡

ወለደቂቃ ፡ ለእንተ ፡ አነ ፡ አፈቅራ ፡ በጽድቅ ።

በሃይማኖት ፡ ጸንተው ፡ ምግባር ፡ ሲሠሩ ፡ ቢገኙ ፡ ለምወዳቸው ፡ ለልጆቿ ፡ ትድረስላቸው ። አንድም ፡ ለኅሪት ፡ ለእንተ ፡ አነ ፡ አፈቅራ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ነው ።

ወበእንተ ፡ ዛቲ ፡ ጽድቅ ፡ አኮ ፡ አነ ፡ ባሕቲትየ ፡ ዘአፍቅራ ፡ አላ ፡ እለኒ ፡ ያአምርዋ ፡ ለጽድቅ ፡ ኵሎሙ ።

ስለዚህም ፡ በሃይማኖት ፡ ጸንታ ፡ ብትገኝ፡ የምወዳት ፡ እኔ ፡ ብቻ ፡ አይደለሁም ። አንድም ፡ እኔ ፡ ብቻ ፡ የምወዳት ፡ አይደለሁም ፡ ሃይማኖትን ፡ የሚያውቋት ፡ ሁሉ ፡ ይወዷታል፡እንጂ ፡ ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፭ ፡ ፩ ። ፫ ፡ ዮሐ ፡ ፩ ።

፪ ፤ ወበእንተ ፡ ዛቲ ፡ ጽድቅ ፡ እንተ ፡ ትነብር ። ኀቤነ ፡ ወትሄሉ ፡ ምስሌነ ፡ ወምስሌነ ፡ ይእቲ ፡ ለዓለም ።

በእንተ ፡ ዛቲ ፡ ጽድቅና ፡ በእንተ ፡ ዛቲ ፡ ጽድቅ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ነው ። ስለዚች ፡ ሃይማኖት ፡ ከጊዜ ፡ እምነት ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ሞት ፡ በኛ ፡ ጸንታ ፡ ስለምትኖር ፡ (ወትሄሉ)፡ ከዕለተ፡ ሞት ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ምጽአት ፡(ወምስሌነ፡ ይእቲ)፡ ከምጽአት፡ በኋላ ፡ በኛ ፡ ጸንታ ፡ ስለምትኖር ፡ ሃይማኖት ፡ የምወዳት ፡(አኮ)፡ እኔ ፡ ብቻ ፡ አይደለሁም ፡

፫ ፤ ሞገስ ፡ ወምሕረት ፡ ወሰላም ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ።

ከእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ዘንድ ።

ወእምኀበ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ወልዱ ፡ ለአብ ፡ እግዚአብሔር ።

የእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ የባሕርይ ፡ ልጁ ፡ ከሚሆንም ፡ ከኢየሱስ፡ክርስቶስም፡ዘንድ፡ ባለሟልነት ፡ ቸርነት ፡ ፍቅር ፡ አንድነት ፡ ይደረግላችሁ ።

ምስለ ፡ ጽድቅ ፡ ወተፋቅሮ ።

ከሃይማኖት ፡ ከምግባር ፡ ጋራ ። ሐተታ ፡ ሞገስ ፡ ምሕረት ፡ ሰላም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የሚገኙ ፡ ናቸው ፡ ጽድቅ ፡ ተፋቅሮ ፡ ከሰው ፡ የሚገኙ ፡ ናቸው ።

፬ ፤ ተፈግሕኩ ፡ ጥቀ ፡

እጅግ ፡ ደስ ፡ አለኝ ፡

እስመ ፡ ረከብኩ ፡ እምደቂቅኪ ፡ እለ ፡ የሐውሩ ፡ በጽድቅ ፡

ከልጆችሽ ፡ በሃይማኖት ፡ ጸንተው ፡ ምግባር ፡ ሲሠሩ ፡ አግኝቻለሁና ። አንድም ፡ ስለ ፡ አገኘኋቸው ፡

በከመ ፡ ነሣእነ ፡ ትእዛዘ ፡ እምኀበ ፡ አብ ፡ ...

ከአብ ፡ ዘንድ ፡ ትእዛዙን ፡ እንደ ፡ ተቀበልነ ፡ የሐውሩ ፡ በጽድቅ ፡ ላለው ።

፭ ፤ ወይእዜኒ ፡ እስእለኪ ፡ እእግዝእት ፡

እመቤቴ ፡ አሁንም ፡ እማልድሻለሁ ፡

ወአኮ ፡ ትእዛዘ ፡ ሐዲሰ ፡ ዘእጽሕፍ ፡ ለኪ ፡

እንግዳ፡ ትእዛዝንየምጽፍልሽ፡ አይደለም፡

አላ ፡ ትእዛዘ ፡ ብሉየ ፡ እንተ ፡ ብነ ፡ ትካት ።

ቀድሞ፡ የነበረች፡ ትእዛዝን፡ ነው፡ እንጂ ። አንድም ፡ ትእዛዝ ፡ ሐዲስ ፡ የምጽፍልሽ ፡ እንግዳ ፡ ትእዛዝ ፡ አይደለችም ፡ ቀድሞ ፡ የነበረች ፡ ናት ፡ እንጂ ፡

ከመ ፡ ንትፋቀር ፡ በበይናቲነ ።

እርስ ፡ በርሳችን ፡ ፍቅርን ፡ እንይዝ ፡ ዘንድ ፡ በጥንተ ፡ ስብከት ፡ የተቀበልናት ፡ ትእዛዝ ፡ ናት ፡ እንጂ ፡ እንተ ፡ ብነ ፡ ላለው ፡ ፩ ፡ ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፯ ።

፮ ፤ ወዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ተፋቅሮትነ ፡

ፍቅር ፡ መያዛችንም ፡ ይህች ፡ ናት ፡

ከመ ፡ ንሑር ፡ በትእዛዙ ፡

በትእዛዙ ፡ ጸንተን ፡ እንኖር ፡ ዘንድ ፡ ነው ። አንድም ፡ እንኖር ፡ ዘንድ ፡ እንጂ ፤ ነው ፡ እንድንኖር ፡ መሆን ፡ ፈቃዱ፡ ነው፡ እንድንኖር ፡ መሆን ፡ ነው ፡

ወዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ትእዛዝ ፡

ትእዛዙም ፡ ይህች ፡ ናት ፡

ከመ ፡ ንሑር ፡ ባቲ ፡

ጸንተን ፡ እንኖርባት ፡ ዘንድ ፡

እንተ ፡ ሰማዕክሙ ፡ ትካት ፡

በጥንተ ፡ ስብከት ፡ የሰማችኋት ፡ ናት ።

፯ ፤ እስመ ፡ ብዙኃን ፡ መስሕታን ፡ እለ ፡ መጽኡ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ እለ ፡ ኢየአምኑ ፡ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ ፡ ከመ ፡ መጽአ ፡ በሥጋ ፡

ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በሥጋ ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ የማያምኑ ፡ ብዙ ፡ ሐሰተኞች ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ተነሥተዋልና ፡

ወዝውእቱ ፡ መስሐቲ ፡ ሐሳዌ ፡ መሲሕ ፡

በመሲሕ ፡ በክርስቶስ ፡ የሚያብል ። አንድም ፡ መሲሕ ፡ ክርስቶስን ፡ የሚያሳብል ፡ (አለ) ፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የማያምን ፡ ሐሰተኛ ፡ መምህር ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ፩ ፡ ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፲፰ ፡ ና ፡ ፬ ፡ ፩ ፡

፰ ፤ ዑቁ ፡ ርእሰክሙ ፡ ኢትሕጒሉ ፡ ዘገበርክሙ ፡

በሠራችሁት ፡ ሥራ ፡ ዋጋችሁን ፡ እንዳታጡ ፡ ለራሳችሁ ፡ ዕወቁ ፡

አላ ፡ ከመ ፡ ዐስበ ፡ ፍጹመ ፡ ትንሥኡ ፡

ፍጹም፡ ዋጋችሁን፡ ታገኙ፡ ዘንድ፡ እንጂ ፡ አንድም ፡ ለራሳችሁ ፡ ዕወቁ ፡ (ወኢትሕጒሉ) ፡ በሠራችሁትም ፡ ሥራ ፡ ዋጋችሁን ፡ እንዳታጡ ፡ ሁኑ ፡ ፍጹም ፡ ዋጋችሁን ፡ እንድታገኙ ፡ ሁኑ ፡ እንጂ ፡ ገላት ፡ ፬ ፡ ፲፩ ።

፱ ፤ ኵሉ ፡ ዘይናፍቅ ፡ ወኢይነብር ፡ በትምህርቱ ፡ ለክርስቶስ ፡ ኢሀሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስሌሁ ፡

የሚጠራጠር ፡ ክርስቶስ ፡ ባስተማራት ፡ በወንጌል ፡ ጸንቶ ፡ የማይኖር ፡ ሁሉ ፡ እግአዚብሔር ፡ አብ ፡ አላደረበትም ፡

ወዘሰ ፡ ይነብር ፡ በትምህርቱ ፡ ለክርስቶስ ፡ በአብ ፡ ወበወልድ ፡ ሀሎ ፡

በክርስቶስ ፡ ትምህርት ፡ በወንጌል ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ ግን ፡ አብን ፡ ወላዲ ፡ ወልድን ፡ ተወላዲ ፡ አብን ፡ ዓለም ፡ ቦታ፡ ወልድን ፡ ዓለም ፡ ቦታ ፡ በማድረግ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራል ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ እንዳለች፡ በማመን፡ ይኖራል፡ ፩፡ ዮሐ፡ ፪፡ ፳፪።

www.ethiopianorthodox.org

፲ ፤ ወዘኒ ፡ ይመጽእ ፡ ኀቤክሙ ፡

በመምህርነት፡ ወደ፡ ፍንተ ፡የመጣ፡ ሰው፡ ቢኖር ፡

ወዘንተ ፡ ትምህርተ ፡ ኢያመጽእ ፡

ይህን ፡ ትምህርት ፡ የማያስተምረውን ፡

ኢታብእዎ ፡ ቤተክሙ ፡

በቤታችሁ ፡ አትቀበሉት ፡

ወባሕቱ ፡ ተቀ ፡ ኢትበልዎ ፡

ቸር ፡ ዋልኽ ፡ ቸር ፡ አደርኽ ፡ ስንኳን ፡ አትበሉት ። ሐቶታ ፡ ምነው ፡ አውሬ ፡ ይብላው ፡ ወንበዴ ፡ ይቀጥቅጠው ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ራት ፡ መብራት ፡ ቦታ ፡ ሰጥቶ ፡ አለማነጋገር ፡ ነው ። (ጥቅ) ፡ ለእመ ፡ ረከብከ ፡ ሰብአ ፡ በፍኖት ፡ ኢትጸብሖ ፡ ወለእመ ፡ ተጸብሐከ ፡ ኢታውሥእ ፡ እንዲል ፡ ፪ ፡ ተሰ ፡ ፫ ፡ ፯ ።

፲፩ ፤ እስመ ፡ ዘይቤሎ ፡ በሐ ፡ ይሳተፍ ፡ በምግባሩ ፡ እኩይ ፡

ቸር ፡ ዋልኽ ፡ ቸር ፡ አደርኽ ፡ የሚለው ፡ በክፉ ፡ ግብሩ ፡ ይመስለዋልና ።

፲፪ ፤ ወብዙኀ ፡ብየ ፡ ዘእጽሕፍ ፡ ለክሙ ፡

የምጽፍላችሁ ፡ ብዙ ፡ ነበረኝ ፡

ወኢፈቀድኩ ፡ በክርታስ ፡ ወበማየ ፡ሕመት ፡

ነገር ፡ ግን ፡ በብራና ፡ በጥቁር ፡ ቀለም ፡ አለ ፡ ብርዕ ፡ ቀርጬ ፡ ቀለመ ፡ በጥብጬ ፡ ብራና ፡ ዳምጬ ፡ ልጽፍላችሁ ፡ አልወደድሁም ፡

እስመ ፡ እትአመን ፡ ከመ ፡ እመጽእ ፡ ኀቤክሙ ፡

ወደ ፡ ፍንተ ፡ እንድመጣ፡ (መጥቼ ፡ ቢል)፡

አፈ ፡ በአፈ ፡ እትናገረክሙ ፡

ቃል ፡ ለቃል ፡ እንድነግራችሁ ፡ አምናለሁና ፡

ከመ ፡ ፍጹመ ፡ ይኩን ፡ ፍሥሐክሙ ፡

ተድላ ፡ ደስታችሁ ፡ ፍጹም ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ፫ ፡ ዮሐ ፡ ቍ ፡ ፲፫ ።

፲፫ ፤ ይኤምኁኪ ፡ ደቂቀ ፡ እኅትኪ ፡ ኅሪት ፡

ኅሪት ፡ ስሟ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የእኅትሽ ፡ ልጆች ። አንድም ፡ ኅሪት ፡ እትዋ ፡ ናት ፡ ብሎ ፡ የእኅትሽ ፡ የኅሪት ፡ ልጆች ፡ ቸር ፡ አለሽ ፡ ይሉሻል ፡

ሞገስ ፡ ወተፋቅሮ ፡ ምስሌክሙ ፡

ባለሟልነት ፡ ፍቅር ፡ ይደረግላችሁ ፡

አሜን ፡

ይሁን ።

መልአት ፡ መልእክት ፡ ዮሐንስ ፡ ዳግሚት ።

ሁለተኛዪቱ፡ የዮሐንስ ፡ ክታብ ፡ ደረሰች፡ ተፈጸመች ።

www.ethiopianorthodox.org